BBC LEARNING ENGLISH

# Essential English Conversation

## How can I get to…?
## እንዴት መሄድ እችላለሁ?

*This is not a word-for-word transcript*

**ምህረተስላሴ**
ጤና ይስጥልን። ማንኛውም የእንግሊዝኛ ተማሪ ሊያውቃቸው የሚገቡ የቋንቋ መሰረታዊያን ወደምናቀርብበት Essential English Conversation እንኳን በደህና መጡ። ምህረተስላሴ እባላለሁ። በዚህ ክፍል እንዴት ወደተለያዩ ቦታዎች መሄድ እንደሚቻል ስለሚጠየቅባቸው መንገዶች ይማራሉ።
ሁለት ሰዎች እንዴት ወደ አውሮፕላን ማረፊያ መሄድ እንደሚችሉ ሲነጋገሩ ያዳምጡ።

***Sian***
*How can I get to the airport?*

***Phil***
*You can go by bus or taxi.*

***Sian***
*I'm late. I need a taxi!*

**ምህረተስላሴ**
ንግግራቸውን ካልተረዱት ብዙም አይጨነቁ፤ ውይይቱን ከፋፍለን እንዲለማመዱት እናግዝዎታለን።
የመጀመሪያዋ ተናጋሪ እንዴት ወደ አውሮፕላን ማረፊያ 'airport' እሄዳለሁ? ስትል ጥያቄ አቅርባለች።

*How can I get to the airport?*

**ምህረተስላሴ**
ሁለተኛው ተናጋሪ በአውቶብስ 'bus' ወይም በታክሲ 'taxi' መሄድ እንደምትችል ነግሯታል።

*You can go by bus or taxi.*

**ምህረተስላሴ**
መኪና እየነዱ 'drive' ወይም በባቡር መሄድ 'go by train' እንደሚቻልም መናገር ይችላሉ።

*You can drive.*

*You can go by train.*

**ምህረተስላሴ**
የመጀመሪያዋ ተናጋሪ 'late' ማርፈዷን ልብ አለች። ያዳምጡና ደግመው ይበሉ።


© British Broadcasting Corporation 2018

*I'm late.*

**ምህረተስላሴ**
እናም 'taxi' ታክሲ እንደምትፈልግ 'need' ተናገረች። ያዳምጡና ደግመው ይበሉ።

*I need a taxi!*

**ምህረተስላሴ**
በጣም ጥሩ፤ አሁን ሰዎች ወደተለያዩ ቦታዎች እንዴት መሄድ እንደሚችሉ ሲጠያየቁ በማዳመጥ እርስዎ ካሉት ጋር ያነጻጽሩ።
ቬራ ተራራማ አካባቢ የሚኖሩ ጓደኞቿን ልትጠየቅ ነው። ለመሄድ የወሰነችው በአውሮፕላን 'plane' ነው።

*How can I get to the mountains?*

*You can go by bus or plane.*

*I don't have time. I want to go by plane!*

ሮበርት በቅርብ ርቀት ወዳለችው ከተማ 'next town' መሄድ ይፈልጋል። መኪና ማግኘት ስላልቻለ በባቡር "train" ለመሄድ ወሰኗል።

*How can I get to the next town?*

*You can go by train or drive.*

*I don't have a car, I want to go by train.*

**ምህረተስላሴ**
እሺ፤ አሁን ንግግሩን ደግመን እንሞክረው። የእንግሊዝኛውን አረፍተ ነገሮች ያዳምጡና ደግመው ይበሉ።
እያንዳንዳቸውን ሁለት ጊዜ ያዳምጧቸዋል።

*How can I get to the airport?*
*How can I get to the airport?*

*You can go by bus or taxi.*
*You can go by bus or taxi.*

*I'm late.*
*I'm late.*

*I need a taxi!*
*I need a taxi!*

**ምህረተስላሴ**
በጣም ጥሩ፤ አሁን እንግሊዝኛውን ምን ያህል እንዳስታወሱ እንይ። አረፍተ ነገሮቹን በአማርኛ ያዳምጡና የእንግሊዝኛ ትርጉማቸውን ይበሉ።


© British Broadcasting Corporation 2018

*ወደአውሮፕላን ማረፊያው እንዴት መሄድ እችላለሁ?*
*How can I get to the airport?*

*በአውቶብስ ወይንም በታክሲ መሄድ ትችያለሽ*
*You can go by bus or taxi.*

*ረፍዶብኛል*
*I'm late.*

*ታክሲ ያስፈልገኛል!*
*I need a taxi!*

**ምህረተስላሴ**
በጣም ግሩም፤ እንዴት ወደተለያዩ ቦታዎች መሄድ እንደሚቻል መጠየቅና መመለስ ተምረዋል። እንዴት ወደ አውሮፕላን ማረፊያ መሄድ እንደሚቻል ለምትጠይቀው የመጀመሪያዋ ተናጋሪ ምላሽ በመስጠት ይለማመዱ።

*How can I get to the airport?*
*I'm late. I need a taxi!*

**ምህረተስላሴ**
በጣም ጥሩ፤ አሁን ጠቅላላውን ውይይት አንዴ ያዳምጡና መልስዎን ያመሳክሩ።

***Sian***
*How can I get to the airport?*

***Phil***
*You can go by bus or taxi.*

***Sian***
*I'm late. I need a taxi!*

**ምህረተስላሴ**
በጣም ጥሩ፤ አሁን እንዴት ወደተለያዩ ቦታዎች መሄድ እንደሚቻል በእንግሊዝኛ መጠየቅና መልስ መስጠት ችለዋል። የተማሩትን መለማመድ አይዘንጉ። ጓደኛ ይፈልጉና እንዴት ወደተለያዩ አካባቢዎች መሄድ እንደሚቻል በእንግሊዝኛ በመጠየቅ ልምምድ ያድርጉ። ለተጨማሪ የኢንሴንሻል ኢንግሊሽ መሰናዶ በሚቀጥለው ክፍል ይጠብቁን። ሰላም ሁኑ!


© British Broadcasting Corporation 2018